ሠላም ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!

# ግንቦት7 ንቅናቄ አሰባሳቢ መሪ ወይስ የፖለቲካ አሣነባሪ ?

በአዜብ ጌታቸው

ዘወትር በሃገራችን ወቅታዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ዙሪያ ለምናዣብብ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ የሰሞኑ ፍሪዳ የግንቦት7 ንቅናቄ መመስረት ስለመሆኑ እሰጥ አገባ የምንገጥም አይመስለኝም።

አለመታደል ሆኖ እስካሁን ድረስ ምስረታን እንጂ ግንባታን፤ ጅምርን እንጂ ቁጭትን ለማየት አልቻልንም።ዛሬም አዲሱ ወሬያችን ስለ ሌላ አዲስ ጅምር ነው። አሁን አሁንማ ስለ ምስረታና በአጠቃላይ ስለ ጅምር እንቅስቃሴ መስማት በራሱ ያሳቅቀኝ ጀምሯል። ጅምር እንቅስቃሴ ይፋ በሆነ ማግስት የሚደለቅ ከበሮና የሚረገጥ ዳንኪራም ብዙም አልጥምሽ ብሎኛል። ወድጄ አይደለም! እባብ ያየ በልጥ በረየ፤ ነውና ጎልብተው አካል ሳይሰሩ ገና በሽልነታቸው ያለመግባባት ሾተላይ ያጠናፈራቸውን በርካታ ጭንጋፍ ጅምሮችን በማየቴ ነው።

ይሁንና ሕልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም እንዲሉ፤ ተስፋ የሚሏትም ነበልባል ትዳከም እንደሆን እንጂ ከስማ የምትቀር አይደለችምና፡ ዛሬም የግንቦት7 ንቅናቄን መመስረት ያየሁት ውስጤ ጭል... ጭል... በምትለው የተስፋ ብርሃን እየታገዝኩ ነው፡፤

ከ10 ውርዴ በኋላ ለ11ኛ ግዜ በመጸነሷ "**አንቺ ሴት ዘንድሮም ተስፋ አልቆረጥሽ?**" ቢሏት "**ማን ያውቃል ...? ይሂስ ቢሆን ጧሪዬ**" እንዳለቺውና 11ኛው ጽንሷ ለፍሬ እንደበቃላት እናት፡-፡፤ እኔም ማን ያውቃል ግንቦት7 መልካም ነገር ፈንጣቂ ቢሆንስ....? በሚል ተስፋን በተስፋ በሰነቀ፤- ጥያቄ አዘል ስሜት ውስጥ ሆኜ ነው ይህንን ጽሁፍ የጻፍኩት።

ለነገሩ ግንቦት7 ድንገት የተከሰተ የአንድ ጀንበር ውልድ አይደለም፡፤ ስለ ዕለተ ውልደቱና አወላለዱ ባናውቅም ጽንስ ስለመኖሩ ግን በነ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ አቅጣጫ አመላካች ጽሁፍ ውስጥ የተመለከትን ይመስለኛል። እኔንም ለመጀመሪያ ግዜ ከማጀት ወደ አደባባይ ያወጣኝና ከአንባቢነት ወደ ተሳታፊነት ያሸጋገረኝ በአቶ አንዳርጋቸው ጽሁፍ ዙሪያ በተንሸራሸረው ውይይት የግሌን አስተያየት ያቀረብኩበት አጋጣሚ መሆኑ የቅርብ ግዜ ትዝታዬ ነው። ነገርን ነገር እያነሳው አቅጣጫዬን ሳልስት ወደ ዋናው ጉዳይ ልመለስ።

አዎ! ወደ ዋናው ጉዳይ ማለትም ወደ ግንቦት7 ንቅናቄ ምስረታ ስመለስ፡- የንቅናቄው ምስረታ ያለተጠበቀ ወይም ነጮቹ እንደሚሉት "Surprise" አልሆነብንም ።ምክንያቱም ቢያንስ ቢያንስ አቶ አንዳርጋቸውና አቶ በእውቀቱ ለንባብ ባበቁት ጽሁፍ ፤ወያኔ ኢህአዴግ እየሰፈረ የሚሰጠን የመብት ድርጎ አላማችንን ከግብ ለማድረስ በቂ አይደለምና የትግል አቅጣጫ ለውጥ ማድረግ እንዳለብን አሳስበውናል፡፤ አቶ አንዳርጋቸውና ባልደረባቸው ማሳሰቢያውን ተከትሎም ስለዝርዝር አፈጻጸሙ የምንለው አለ ብለውን እየጠበቅን እያለ የግንቦት7 ውልደት ይፋ መሆን ምናልባት ወደ ተግባር የሚገባበትን ግዜ ከጠበቅነው ትንሽ ቀደም አርጎት ይሆን እንጂ ያልተጠበቀ አልነበረም ለማለት ነው።

የአቶ አንዳርጋቸው ጽሁፍ በወጣበት ሰሞን ከአንድ ወዳጄ ጋር ስለዚሁ ጽሁፍ ስንወያይ ያለኝ ነገር አሁን ሳየው በጣም አስተዋይነት የተሞላበት አስተያየት ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፤ ጽሁፉ ለንባብ ቀርቦ፡- ገሚሱ *ጦርነት አንሻም* እያለ በጸሃፊዎቹ ላይ ተቃውሞውን ሲያዥጎደጉድ ገሚሱ ደግሞ *ወያኔ ሰላም ብሎ ነገር አይገባውምና አቶ አንዳርጋቸው ልክ ናቸው* እያለ መግባባት የሌለበት እሰጥ አገባ መጧጧፉን ያስተዋለው ይህ ወዳጄ፡- ጽሁፉን በደንብ አንብቦ ካጣጣመ በኋላ፡-በሰጠው አስተያየት " **ከዚህ ጽሁፍ የተረዳሁት አቶ አንዳርጋቸው የሃገራቸው ችግር እልባት ሳያገኝ እንቅልፍ የማይተኙ አይምሯቸውም እረፍት የማያደርግ ውድ ዜጋ መሆናቸውን ፡ ጽሁፋቸውም ትናትን በተገቢው የገመገመ ዛሬንም ያየ ነገንም በማመላከት ረገድ የበኩላቸውን ያቀረቡበት ነው፡፤**

ሠላም ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!

**ይሁንና እንዲህ አይነት ሰፊና ጥልቅ የሆነ ጥናትና ምርምር የተደረገበት ሥራ አደባባይ አውጥተው ተወያዩበት ማለታቸው ትክክለኛ አካሄድ አይመስለኝም። እንደኔ እንደኔ ጽሁፉን በሳቸው የፖለቲካ ንቃትና ብስለት ደረጃ ከሚገኙና እንቅስቃሴውን ይደግፋሉ ከሚሏቸው ሰዎች ጋር ተወያይተውበት የሚጨመር ጨምረው የሚቀነስ ቀንሰው ካበሰሉት በኋላ ለተግባራዊነቱ ስምምነት ላይ ሲደርሱ አላማቸውን ከነፕሮግራማቸው ይዘው ወደ ሕዝብ መቅረቡ የበለጠ ቀና ይመስለኛል ፤" ነበር ያለኝ።**

በርግጥም በተከታይ ሲጠበቅ የነበረው የአቶ አንዳርጋቸው ጽሁፍ የግንቦት7 ውልደትን ይዞ ብቅ ማለት የወዳጄን አርቆ አስተዋይነት በጨረፍታም ሳያሳይ አልቀረም እላለሁ(ቢያንስ ለኔ አሳይቶኛል)፡፤ ይህ ባይሆን ኖሮ በረቂቅ ጽሁፍ ስንዳረቅ ጀንበር ጥልቅ ብላ በቀረች ነበር፡፤በነገራችን ላይ ለግንቦት7 ምስረታ አቶ አንዳርጋቸው ከሁሉም በላይ ሚና ተጫውተዋል የሚል እሳቤ እንደሌለኝ እንድታውቁልኝ እሻለሁ፡፤ እኔ ለመግለጽ የፈለኩት የግንቦት7 ምስረታ ያልተጠበቀ ያልሆነው እሳቸውና አቶ በእውቀቱ ባቀረቡልን ጽሁፍ ላይ በተገኘው ፍንጭ መሆኑን ለማመላከት ብቻ ነው። ለነገሩ አቶ አንዳርጋቸው ሃሳባቸውን ለሕዝብ ማውጣታቸው እንጂ ዶ/ር ብርሃኑን ጨምሮ ሌሎቹም የንቅናቄው መስራቾች በየበኩላቸው ጉድ ጉድ ሲሉ እንደከረሙ ግንቦት7 ራሱ ይፋ አድርጎታል።

አሁንም ወደ ዋናው ነጥብ ወደ ግንቦት7 ምስረታ ልመለስ፡፤ የግንቦት7 ምስረታ ይፋ መሆንን ተከትለው በአብዛኛው ኢትዮጵያዊ አይምሮ የሚነሱ ጥያቄዎች በርካታ ይመስሉኛል። ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ ያህል፦

- የግንቦት7 ንቅናቄን መመስረት ሕዝብ የሚቀበለው እንዴት ነው?
- ሌሎችስ ተቃዋሚ ድርጅቶች እንዴት ያዩታል ?
- የግንቦት7 ንቅናቄ እንቅስቃሴዎች በሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶች እንቃስቃሴ ላይ የሚያሳድረው አሉታዊና አዎንታዊ አንድምታ ምን ይሆናል? የሚሉት ይመስሉኛል። የንቅንናቄውም ስኬታማነት እነዚህ ጥያቄዎች በሚኖራቸው ምላሾች ላይ የተመሰረተ ነው ብዬ አስባለሁ፡፤

ቀጥዬ ንቅናቄው እንደ አላማ ካስቀመጠው ማንፌስቶውና በመሪዎቹ ከተሰጠው መግለጫ በመነሳት የግሌን አስተያየት ለማስቀመጥ እሞክራለሁ፡፤

1ኛ/ንቅንናቄውን ሕዝብ እንዴት ይቀበለዋል? የሚለው ጥያቄ ምላሽ ብዙም አወዛጋቢ የሚሆን አይመስለኝም፡፤ ምክንያቱም ሕዝብ አፋኙን የወያኔ አስተዳደር ከጫንቃው ላይ ለማውረድ በነጠላም ሆነ በቡድን፤ በሕብረትም ሆነ በውህደት የሚንቀስቀሱትን ሁሉ ሲደግፍ እንደቆየ ሁሉ፤ ለግንቦት7 እንቅስቃሴ ስምረትም የበኩሉን ድጋፍ መስጠቱ የሚጠበቅ በመሆኑ ነው፡፤(ሕዝብ ስል በየትኛውም የፖለቲካ ድርጅት አባል ያልሆነውን ስብስብ ማለቴ ነው፡፤ ምክንያቱም የፖለቲካ ድርጅት አባላት ለንቅናቄው የሚኖራቸው አመለካከት ድርጅታቸው ለንቅናቄው የሚኖረው አመለካከት ስለሚሆን በሁለተኛው ጥያቄ የሚታይ ይሆናል።)

2ኛ/ ንቅናቄውን ሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶችስ እንዴት ያዩታል? የዚህ ጥያቄ ምላሽ ዋናውና ምናልባትም የንቅናቄውን እንቅስቃሴ ብቻም ሳይሆን በአጠቃላይ ለዲሞክራሲያዊ ሥርአት ግንባታ የሚደረገውን እንቅስቃሴ ስኬታማነት አልያም ውድቀት የሚወስን ይመስለኛል።(አሁንም ሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶች ስል በወያኔ መንግስት የሰላማዊ ትግል መስፈርት ተለጉሞ መንቀሳቀስ የትም አያደርስም! ብለው እየተንቀሳቀሱ ያሉትን ድርጅቶች ነው፡፤ ይህን ያልኩበት ምክንያት በዚህ ወቅት በሰላማዊ መንገድ አገር ውስጥ ሆነው ወያኔን የሚታገሉ አካሎች ለግዜውም ቢሆን ከመርህ አንጻር ከንቅናቄው እንቅስቃሴ ጋር ሊቆራኙ ያለመቻላቸውን ከግንዛቤ በማስገባት ነው፡፤ )

በበኩሌ፦ ሌሎች ተቃዋሚዎች ንቅናቄውን እንዴት ያዩታል? የሚለውን ጥያቄ በግሌ

ሠላም ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!

ልመልስ ብዬ አልገበዝም። ምክንያቱም ሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶች ለንቅናቄው የሚኖራቸው አመለካከት በራሳቸውና በራሳቸው ብቻ! በሂደት የሚገለጽ እንጂ በአንድ ግለሰብ የሚተነበይ አለመሆኑን ጠንቅቄ ስለማውቅ ነው፡፤ እኔ ላነሳሳ የምሻው እንደ ማንኛውም ቀና-አሳቢ ኢትዮጵያዊ ተቃዋሚ ድርጅቶች ንቅናቄውን በቀና መልክ እንዲያዩ የሚረዱ የመሰሉኝን ነጥቦች ነው።

ሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶች ንቅናቄውን እንዴት ይቀበሉት ይሆን ? የሚለው ጥያቄ በአይምሮዬ መጉላላት እንደ ጀመረ በጥቂቱም ቢሆን ግንዛቤ ቢሰጠኝ ብዬ የአንድ ተቃዋሚ ድርጅት አባል መሆኑን የማውቀውን ሰው አስተያየት ጠይቄው የሰጠኝን ምላሽ እዚህ ላይ ማንሳቱ ተገቢ ይመስለኛል። በነገራችን ላይ ግለሰቡ የሰጠኝ አስተያየት የግሉ አስተያየት እንጂ ድርጅቱ ስለ ግንቦት7 ያለው አስተያየት ስለመሆኑ ምንም ማረጋገጫ የለኝም፡፤ ይሁንና ለማነሳው ነጥብ አጋዥ ገላጭነት አይጠፋውምና የግለሰቡን አስተያየት ቀጥሎ እንዳለ አቀርበዋለሁ፡፤ .

ጥያቄዬ የግንቦት7 ንቅናቄን እንዴት አገኘህው ? የሚል ነበር። የሰጠኝም መልስ፦ " ግንቦት7 ንቅናቄ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ውቂያኖስ ውስጥ እንደ አሸን የፈሉትን የፖለቲካ ድርጅቶች ሊውጥ የተነሳ ግዙፍ የፖለቲካ አሳነባሪ ነው ፡፡" የሚል ነበር፡፤ ንቅናቄውን የፖለቲካ አሳነባሪ ብሎ መሰየሙ አስገርሞኝ ሃሳቡን የበለጠ ለመረዳት እንዴት? የሚል ጥያቄዬን አስከተልኩ።
እሱም መልሶ " አየሽ አሣነባሪ በየአቅጣጫው የሚሽሎኮሎኩትን ሚጢጢዬ አሳዎች በነጠላ አሳዶ መብላት አስቸጋሪ ስለሚሆንበት አፉን ብቻ በስፋት ከፍቶ ይጓዛል፡፤ አሳዎቹ በራሳቸው ግዜ እየዋኙ መጥተው አፉ ውስጥ ይገባሉ። የሱ ሥራ ገብተው ሲያበቁ አፉን መዝጋት ብቻ ነው፡፤ ግንቦት7 ንቅናቄም በኢትዮጵያ የፖለቲካ ውቂያኖስ ውስጥ በየአቅጣጫው የሚሙለጨለጩትን የፖለቲካ ድርጅቶች በተናጠል አነጋግሮ ወደ አንድ ስምምነት ላይ ለማድረስ አስቸጋሪ እንደሆነ የሚያውቁት መስራቾቹ ማንም ሊቃወመው ወይም ልዩነት አለኝ ሊል በማይችልበት መልክ ሰፊ ፕሮግራማቸውን በመቅረጽ ሁሉንም ለመጠቅለል ነው የተነሱት" ሲል ሃሳቡን አጠቃለለ።

ከዚህ አስተያየቱ የተረዳሁት ነገር በንቅናቄው እንቅስቃሴ እንዋጣለን የሚል ሥጋት እንዳለ ነው፡፤ ሥጋቱ ግን የንቅናቄውን መርህና አላማ ካለመረዳት የመነጨ ሳይሆን ካለማመን የመነጨ መሆኑን በቀጣይ ባደረግነው ውይይት ተረድቻለሁ።

አሳነባሪውና ትናንሾቹ አሳዎች ያላቸው ግንኙነት የአጥማጅና የተጠማጅ እንጂ ግንቦት7 ንቅናቄ ከሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር ይኖረኛል እንደሚለው የባልደረብነት ግንኙነት አለመሆኑን በማንሳት ምሳሌውን እንደገና እንዲመረምረው ጠይቄው ነበር፡፤ በኋላም ከጥርጣሬ በስተቀር በምክንያት የተደገፈ ምላሽ ሊሰጠኝ አለመቻሉን ገለጸልኝ። በነገራችን ላይ ከግለሰቡ ጋር ሰፊ ውይይት አድርገን ወደ አንድ እምነት የደረስን ይመስለኛል ፡፤ ነገ ድርጅቱ ምን አቋም ሊይዝ እንደሚችል ባላውቅም ማለቴ ነው፡፤

እሱ በአሣነባሪ የመሰለውን የግንቦት7 ንቅናቄንና መሪዎቹን እኔ ደግሞ አዲስ የባቡር ሃዲድ ዘርግተው የባቡሩን መሪ በመያዝ ተቀጣይ ፉርጎ በሚጠብቁ የባቡር ሹፌሮች በመመሰል ያቀረብኩለት ምሳሌ ነበር ያስማማን። ምሳሌውን በዚህ ላቁምና ከንቅናቄው ማንፌስቶና መግለጫ በመነሳት አዎንታዊ ገጽታዎቹን ለማመላከት ልሞክር;

ንቅናቄው ይፋ እንዳደረገው እንቅስቃሴው የሚዘልቀው በሕዝብ ይሁኔታ ዲሞክራሲያዊ መንግስት እስኪመሰረት ድረስ ነው፡፤ ማለትም የንቅናቄው የትግል ጉዞ የሃገራችን ሕዝብ ይሆነኛል ያለውን መርጦ በመንግስትነት በሰየመበት ቅጽበት የሚያበቃ እንደሆነም ተግልጿል፡፤ ይህ ንቅናቄ በዲሞክራሲ በፍትህና በነጻነት የሚያምን ዜጋ ሁሉ በአባልነት ሊቀላቀለኝ ይችላል ሲል ግልጽና አርበ ሰፊ መመዘኛም አውጥቷል፡፤

ሌሎች ድርጅቶች ንቅናቄውን እንዴት ሊያዩት ይገባል የሚለውን መነሻ ጥያቄ መልስ

ሠላም ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!

በግልጽ ለማስቀመጥ እንዲረዳኝ የንቅናቄው ጉዞ እሰከ ሕዝባዊ መንግስት ምስረታ ድረስ ተብሎ በይፋ መገደቡና የአባልነት መስፈርቱም አብዝኛውን ዜጋ ሊያቅፍ በሚችል መልኩ መቀረጹ ፋይዳው ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ ተመልክቼ ማለፍ እሻለሁ።

ከትግል ልምዳችን እንደምንረዳው አብዛኛው ተቃዋሚ ድርጅት የሚያደርገው እንቅስቃሴ ሁለት መልክና ክፍል የያዘ ነው። 1ኛው ክፍል አምባገነኑንና ኢ-ዲሞክራሲያዊውን የወያኔን አስተዳደር ከሕዝብ ጫንቃ ላይ ለማውረድ የሚደረግ እንቅስቃሴ ሲሆን 2ኛውና ዋናው ማለትም ፕሮግራሙን የሚቀርጽበት እንቅስቃሴ ደግሞ ከአምባገነኑ የወያኔ መንግስት መወገድ በኋላ ለሚመሰረተው መንግስት እራሱን እጩ አድርጎ የሚያቀርብበት ብሎም የሕዝብን ይሁኔታ አግኝቶ በትረ ስልጣኑን የሚጨብጥበትን አላማ የያዘ የትግል እንቅስቃሴ ነው፡፤ይህን ሁለት ክፍል በቀላሉ ለመለየት እንዲያመቸን ስልጣን ለማስለቀቅና ስልጣን ለመጨበጥ የሚደረግ ትግል ብለን ልንከፍለው እንችላለን፡፤

ከዚህ በመነሳት ስመለከተው የግንቦት7 ንቅናቄ እንቅስቃሴ እሰከ ሕዝባዊ መንግስት ምስረታ ድረስ ተብሎ በይፋ መገደቡ ትልቁ ጠቀሜታው አብዛኛው ተቃዋሚ የሚጋራውን ማለትም አምባ ገነኑን መንግስት ስልጣን ለማስለቀቅ(በሰላምም ሆነ በሌላ መንገድ) የሚደረገውን ጉዞ አብሮ እንዲጓዝ ማስቻሉ ነው፡፤

ተቃዋሚዎች ኢ-ፍትሃዊ ኢ-ዲሞክራሲያዊና የዜጎች ነጻነት ያልተከበረበትን አስተዳደር ማስወገድ የጋራ አላማቸው ስለሚሆን በዚህ ጎዳና ያለምንም ልዩነትና ችግር የሰመረ ጉዞ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፤ የክፍል አንድ የትግል ጉዞ በውጤት ከተጠናቀቀ በኋላ የሚቀጥለው የክፍል ሁለት የትግል ጉዞ ሕዝብ ይሆነኛል የሚለውን የፖለቲካ ድርጅት በመንግስትነት የሚሰይምበት ወይም ሕዝባዊ መንግስት የሚመሰረትበት ጉዞ ነው።በዚህ በሁለተኛው ጉዞ ላይ የመጀመሪያውን የጉዞ ክፍል አብረው የተጓዙ የፖለቲካ ድርጅቶች የጋራ ጉዟቸው ያበቃና በየግላቸው የሕዝብን ይሁኔታ ያስገኝልናል ብለው በነደፉት ፕሮግራም መሰረት ተንቀሳቅሰው በለስ የቀናውና በሕዝብ የተመረጠው ድርጅት በትረ ሥልጣኑን ይረከባል ማለት ነው፡፤

እንግዲህ የግንቦት7 ንቅናቄም ጉዞ ይህ በሕዝብ የተመረጠው ድርጅት በትረ ስልጣኑን ተረክቦ መሃላ በፈጸመበት ቅጽበት የሚያበቃ መሆኑ ግልጽ ሆኗል፡፤ ይህ ማለት ደግሞ ግንቦት7 ንቅናቄ ፍትሃዊ ሥርአትን ከመመስረት ባሻገር ምንም የስልጣን አላማ እንደሌለው ግልጽ ያደረገ በመሆኑ የሥልጣን አላማ ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች ይህን ንቅናቄ በጥርጣሬ ሊያዩበት የሚችሉበት ምንም ምክንያት አይኖርም ባይ ነኝ።

አሁንም ከትግል ልምዳችን እንደምንረዳው፦ተቃዋሚዎች በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠው ሲያደርጉት የነበረው ልዩነትን የማጥበብ ሙከራ ሁሉ እየከሸፈ ጭራሽ ወደባሰ ቅራኔ ውስጥ ሲከታቸው የቆየው ኢ-ዲሞክራሲያዊው አስተዳደር ከተወገደ በኋላ ሊደረጉ የሚገባቸውን አላስፈላጊ ውይይቶች ከወዲሁ በማንሳት እንደሆነ የቅርብ ግዜ ትዛታችን ነው። በዚህም ረገድ የግንቦት7 ንቅናቄ የስምምነት ነጥቦችን በማጥበብ በተቃዋሚዎች መካከል ወቅታቸውን ያልጠበቁ ልዩነቶች እንዳይጫሩ ያደርጋል ባይ ነኝ፡፤በርግጥ በግርድፉ ሲታይ ቀላልና ስሙር የሚመስለው ይህ አገላለጽ፦ በሂደት ሲፈተን በርካታ መሰናክሎች እንደሚገጥሙት አይጠፋኝም፡፤ ነገር ግን እንደ መነሻ በግንቦት7 ንቅናቄ ተቀርጾ የቀረበው የጉዞ አቅጣጫ (ሃዲድ) ሁሉንም ተቃዋሚ ድርጅት አቻችሎ እስከ ዲሞክራሲያዊ ሥርአት ግንባታ ድረስ ላለው ጉዞ ሊኖራቸው የሚገባውን የቁርኝት ይዘት በትክክል ያሰቀመጠ መሆኑን መናገር የሚቻል ይመስለኛል።

**<u>3ኛውና የግንቦት7 ንቅናቄ እንቅስቃሴዎች በሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶች እንቃስቃሴ ላይ የሚያሳድረው አሉታዊና አዎንታዊ አንድምታ ምን ይሆናል?</u>**

ባልሳሳት የግንቦት7 ንቅናቄ አመራሮች ትልቅ ሥራ የሚጠብቃቸው በዚህ ጥያቄ ዙሪያ ይመስለኛል። ለግዜው ይህንን ጥያቄ በተመለከተ ሌላ ግዜ ልመለስበትና የዛሬውን ጽሁፍ በዚሁ ልቋጭ፡፤